# የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ሞዴል መመሪያ ቁጥር 701/2013 (ተሻሽሎ የቀረበ)

Industrial Extension Service Delivery Model Directive No. 701/2013 (Revised Version)

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር
Ministry of Urban Development and Construction

ግንቦት 14፥ 2010

# መግቢያ

መንግሥት በከተሞች የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገትን ለማፋጠን ከቀየሳቸው ስትራቴጂዎች መካከል አንዱ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ በመሆኑና ስትራቴጂውን በብቃት ለመፈጸም ብቁ የሰው ኃይል፣ ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና የአሰራር ስርዓት ወሳኝ ሚና ያላቸው በመሆኑ፣

በሀገሪቱ የሚገኙ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ገበያን መሠረት ያደረጉ እና በጥራት፣ በምርታማነት፣ በጊዜና በዋጋ ተወዳዳሪ የሆኑ ምርቶችንና አገልግሎቶችን ለማቅረብ እንዲችሉ ፍላጎትን መሠረት ያደረገ እና በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂው በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር መመሪያ በ2003 ዓ.ም ተዘጋጅቶ ባለፉት አመታት ተግባራዊ በመደረጉ አበረታች ውጤቶች የተመዘገቡ መሆናቸውን መገንዘብ የተቻለ በመሆኑ፣

በየደረጃው ያሉ አስፈፃሚ አካላት ማለትም የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ፣ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲና የአነስተኛ ፋይናንስ አቅራቢ ተቋማት ተቀናጅተው ያላቸውን የሰው ኃይል አቅም በማጐልበትና ሀብታቸውን በማንቀሳቀስ በ2ኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ዘመን ብቁና ተወዳዳሪ ኢንተርፕራይዞች ለማፍራት የድርሻቸውን እንዲወጡ ከአዲሱ የኤጀንሲው ተልዕኮ እና ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ከዚህ ቀደም ይሰራበት የነበረውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ የነበሩትን ክፍተቶች ለመሙላት በሚያስችል መልኩ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ መሰረት

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ መመሪያ የኢንተርፕራይዞችን የዕድገት ደረጃ እና የኤጀንሲውን ተልዕኮ ታሳቢ ያደረገና ወጥነት ያለው ሞዴል መመሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ እንዲሁም በዘርፉ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ በመምጣቱ ካለው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር ለሁሉም ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልገውን ድጋፍ ከኪራይ ሰብሳቢነት የጸዳ፣ አሳታፊ፣ ፍትሃዊና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማቅረብ ይቻል ዘንድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 374/2008 አንቀጽ 14 መሠረት ይህ ሞዴል መመሪያ ተሻሽሎ ተዘጋጅቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ለመስጠት የወጣ ሞዴል መመሪያ ቁጥር **701/2013** ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም እስካልተሰጠው ድረስ በዚህ መመሪያ ውስጥ፤

1) **"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት"** ማለት የኢንተርፕራይዞቹን ችግር የለየና በፍላጎት ላይ የተመሠረተ የተሟላ መረጃ ማደራጀትና የመስጠት፣ ሥልጠና ድጋፍ ፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ ግብይት፣ ምርጥ ተሞክሮ ቅመራና ማስተላለፍን የሚያካትት ድጋፍ ነው፡፡

2) **"ሥልጠና"** ማለት በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት በንግድ ሥራ አመራርና በቴክኒክና ሙያ የሠልጣኞችን አመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት የሚያሳድግና በአዎንታዊ መልኩ የባህሪና የአሰራር ለውጥ የሚያመጣ የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የመማማር ሂደት ነው፡፡

3) **"የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና"** ማለት በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፎች ለተሠማሩና ለሚሠማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ፣ ባለሙያዎች አንድን ምርት ወይም አገልግሎት በብቃት ለማቅረብ ፣ ጥራትና ምርታማነትን በቀጣይነት ለማሻሻል፣ የፈጠራ ሥራዎችን ለማበረታታት አመለካከት፣ ዕውቀትና ክህሎት በማሳደግ በተሰማሩበት ወይም በሚሰማሩበት መስክ ላይ እሴትን በመጨመር ልማትን ለማፋጠን እንዲያስችል የሚሰጥ ሙያዊ ሥልጠና ነው፣

4) **"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የድጋፍ ማዕቀፎች"** ማለት የቴክኒካል ክህሎት፣ የቴክኖሎጂ ድጋፍ፣ የኢንተርፕሩነርሽፕ እና የጥራትና ምርታማነት/ካይዘን/ ድጋፍ የሚያጠቃልል ድጋፍ ማለት ነው፡፡

5) **"ማምረቻ መሳሪያ"** ማለት፡- የተለያዩ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ምርትን ለማምረት እና አገልግሎት ለመስጠት የሚያገለግሉ የተለያዩ በሰው ሐይል ፣ በእንስሳት ጉልበት የሚሳቡ እና በአማራጭ የሃይል ምንጮች የሚሰሩ፣መሳሪያዎችና ማሽነሪዎች ማለት ነው፡፡

6) **"ፈጻሚ አካላት"** ማለት ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት ለመስጠት የተዋቀሩ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና

ምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲዎች፣ አነስተኛ ፋይናንስ ተቋማት እና የካፒታል ፋይናንስ እቃዎች አቅራቢ አክሲዮን ማህበራት ያጠቃልላል።

7) **"የትብብር ስልጠና ስርዓት"** ማለት ሠልጣኙ አብዛኛውን የስልጠና ጊዜ በኩባንያዎች ውስጥ በተግባር እየሰራ የሚሰለጥንበትና ኢንዱስትሪውም ሰልጣኙን በሚፈለገው ደረጃ በማብቃት ለሥራው ብቁ አድርጎ ለማቅረብ የሚቻልበት ዘዴ ሲሆን ተቋማት ከኢንተርፕራይዞች /ቀጣሪ ድርጅቶች ጋር በመሆን በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ የትብብር ሥልጠና የሚያካሄዱበት ሥርዓት ነው።

8) **"የኩባንያ ዉስጥ ስልጠና"** ማለት የኢንዱስትሪው ሠራተኞች ከአዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎች ጋር እንዲተዋወቁ፤ ቴክኖሎጂዎችን አሟጠው በመጠቀምና በማሻሻል ምርታማነትን ብቃትንና ብሎም የኢንዱስትሪውን ዓለም-አቀፋዊ ተወዳዳሪነት ማሳደግ እንዲችሉ ለማድረግ የሚጠቅም የሰው ኃይል ማጎልበቻ የስልጠና ዜዴ ነው።

9) **"ቴክኖሎጂ"** ማለት አንድን ግብዓት በቀላሉ ገበያ ላይ ሊውል ወደሚችል ምርት የመለወጥ ሂደት ሲሆን ቁሳዊ፣ ዕውቀታዊ፣ ሰነዳዊና አደረጃጀት/አሰራር ክፍሎችን ያካተተ ነው።

10) **"የእሴት ሰንሰለት"** ማለት አንድ ለገበያ የሚቀርብ ምርት ከጥሬ ዕቃ ጀምሮ እስከ ፍጆታ እስከዋለበት ጊዜ ድረስ ለምርቱ እስተዋፅኦ የሚያደርጉና እሴቶች የሚጨምሩ ተዋናዮችና የሥራ ሂደቶች የሚተሳሰሩበት ነው።



11) **"የዕሴት ሰንሰለት ትንተና"** ማለት የአንድ ምርት የአሰራር ሂደትን በመዘርዘርና በመተንተን የቴክኖሎጂ ክፍተቶችን በእውቀት፣ በቁስ፣ በአሰራርና በአደረጃጀት በመለየት በአሰራሩ ላይ ክፍተት ያመጣውንና ቢሻሻል የሚያመጣውን ፋይዳ ለይቶ መፍትሄውን የማስቀመጥ ሂደት ነው።

12) **"የአዋጭነት ትንተና"** በእሴት ሰንሰለት ትንተና መሰረት የተለየውን ቴክኖሎጂ አማራጮችን በማፈላለግ ከምርታማነት፣ ከምርት ጥራት፣ ከጉልበት አጠቃቀምና ከወጪ አንፃር ገምግሞ ቴክኖሎጂው ለማምረት፣ ለመግዛት ወይም ለማሻሻል የሚያስችል የአሠራር ሂደት ነው።

13)**"ንድፍ"** ማለት አንድን ቴክኖሎጂ በወጥነት ደረጃውን ጠብቆ እንዲባዛ ለማገዝ የቴክኖሎጂ ስኬትና ምስል፣ የአመራረት ሂደት፣ የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን ዝርዝር የያዘ ሰነድ ነው።

14)**"ቴክኖሎጂ ማቀብ"** ማለት አንድን የተመረጠ ቴክኖሎጂ በብቃትና በዘላቂነት ደረጃውን ጠብቆ ለማሸጋገር የቴክኖሎጂውን ንድፍና ናሙና በማዘጋጀት ፈትሾ የማጠናቀቅ ሥራ ነው።

15) **"ቴክኖሎጂ ሽግግር"** ማለት አንድ የታቀበ ቴክኖሎጂ ፈላጊ ኢንዱስትሪዎችንና አብዥዎችን በመለየትና በማብቃት ቴክኖሎጂውን ከአመንጪዎች ወደ ተጠቃሚዎች የማስተላለፍ ሂደት ነው።

16) **"የሙያ ብቃት ምዘና"** ማለት አንድ ባለሙያ በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መስፈርት መሰረት የሚጠበቅበትን ብቃት መያዙ የሚረጋገጥበት ስርዓት ነው።

17) **"የምርት ሂደት (production process) "** ማለት የሰው ኃይል፣ የተፈጥሮ ሃብትና የማምረቻ መሣሪያን በማቀናጀት ጥሬ ሃብትን ወደ ልዩ ልዩ ምርቶች የመቀየ ወይም አገልግሎት የመስጠት እንቅስቃሴ ነው::

18) **"ምርት (production)"** ማለት በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት እንቅስቃሴ የሚገኝ ተጨባጭ ውጤት ነው::

19) **"ጥራት (Quality)"** ማለት አንድ ምርት በተጠቃሚው ተፈላጊ የሆኑና እንዲሟሉ የሚጠበቁ ልዩ ልዩ መሥፈርቶችን ሙሉ በሙሉ አሟልቶ የመገኘት ብቃት ነው::

20) **"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ"** ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ለኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚሰጥ አሰልጣኝ ማለት ነው::

21) **"የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ፋሲሊቴተር"** ማለት በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚሰጠውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለማመቻቸት የተመደበ የአንድ ማዕከል አገልግሎት ባለሙያ ነው::

22) **"ጠቅላላ ካፒታል"** ማለት ህንፃን ሳይጨምር ከኢንተርፕራይዙ ጠቅላላ የቢዝነሱ ሀብት ላይ ዕዳው ተቀንሶ የሚገኘው ካፒታል ማለት ነው::

23) **"ጥቃቅን ኢንተርፕራይዝ "** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣ የቤተሰብ አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞች ጨምሮ እስከ አምስት ሰዎች





ቀጥሮ የሚያስማራና የጠቅላላ ካፒታሉ መጠን ህንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ወይም በኢንዱስትሪ ዘርፍ ከብር 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው::

24) **"አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ"** ማለት የኢንተርፕራይዙን ባለቤት፣የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ6 እስከ 30 ሰዎች የሚያስማራና የጠቅላላ ካፒታል መጠን ሕንፃን ሳይጨምር በአገልግሎት ዘርፍ ከብር 50,001 (ሃምሳ ሺህ አንድ) እስከ 500,000 (አምስት መቶ ሽህ) ወይም በከተማ ግብርና፣ በባህላዊ ማዕድን ማምረትና በግንባታ ዘርፍ ከብር 100,001 (አንድ መቶ ሺህ አንድ) እስከ 1.5 ሚሊዮን ያልበለጠ ኢንተርፕራይዝ ነው::

25)በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፣

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በኢትዮጵያ ከተሞች በሚገኙ የከተማ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

## 4. ዓላማ

በከተሞች ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት በመስጠት በገበያ ብቁና ተወዳዳሪ ሆነው ሰፊ የሥራ ዕድል እንዲፈጥሩና ገቢያቸው እንዲሻሻል ማድረግ::

## 5. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መርሆዎች

1) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መፈልፈያና የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ፣

2) በገበያ ፍላጎት የሚመራ፣ የተቀናጀና የተዋሃደ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣

3) ግልፀኝነትን፣ ተጠያቂነትን፣ ታማኝነትን እና ተደራሽትን የተላበሰ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት፣

4) የኢንተርፕራይዞች እድገትና ጥቅም የእኔም ጥቅም ነው ብሎ በማመን መንቀሳቀስ፣

5) ለነባርና ሞዴል ኢንተርፕራይዞች ቅድሚያ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መስጠት እንዳለበት አምኖ መንቀሳቀስ፣

6) ቴክኖሎጂን መቅዳትና ማሸጋገር ለኢንተርፕራይዞች ቁልፍ የእድገት መሠረት መሆኑንና ለኢኮኖሚ እድገትም ትልቅ መሳሪያ መሆኑን አምኖ መተግበር



# ክፍል ሁለት

## የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አቅርቦት

## 6. የሰው ኃይል ልማት

የሰው ኃይል ልማት የአመለካከት፣ የዕውቀትና የክህሎት ለውጥ ማምጫ መሳሪያ በመሆኑ የሥልጠና ድጋፍ ከሥልጠና ፍላጎት ዳሰሳ እስከ ሙያ ብቃት ምዘና ድረስ የሚከናወን ዝርዝር ተግባር ነው::

### 1) የሰው ኃይል ገበያ ጥናት (Labour market analysis)

ሀ) የሰው ኃይል ገበያ ጥናት እንደአስፈላጊነቱ በየዓመቱ የናሙና ዘዴ በመጠቀም በተመረጡ የሥራ ዘርፎችና ነባር ኢንተርፕራይዞች በፌደራልና በክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ ይከናወናል፣

ለ) በሰው ኃይል ገበያ ጥናቱ መሰረት ከፌደራል ጀምሮ በየደረጃው የሚገኙ የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤቶች በተዋረድ በጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ የሚሰማራውን የሰው ኃይል በሙያ፣ በደረጃና በብዛት በመለየት አዘጋጅተው ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ይሰጣሉ::

ሐ) ሙያዎችን የመለየትና ሃገር አቀፍ የሙያ ደረጃዎችን የማዘጋጀት ተግባር በፌደራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና አመቻችነት ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን ጨምሮ በሥራ ዓለም ያሉ ባለድርሻዎችና በየኢንዱስትሪ ዘርፉ ባለሙያዎች

መሪነት ይከናወናል። ዓለምአቀፍ ምርጥ ተሞክሮዎችና የሙያ ደረጃዎች በግብዓትነት ይወሰዳሉ።

መ) በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መሰረት የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ቢሮ/ኤጀንሲ ተቋማት የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲን በማሳተፍ ስርዓተ ትምህርትና የማሰልጠኛ ማንዋል ያዘጋጃሉ።

ሠ) ነባር ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መሰረት የሙያ ብቃት ምዘና እንዲያገኙ ማድረግ ክፍተታቸውን ለይቶ ማብቃት፤

## 2) የሥልጠና ቅድመ ዝግጅት

ሀ) በዘርፉ ለተሠማሩና ለሚሰማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ስለ ስልጠና አስፈላጊነትና ጠቀሜታ በተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎች በመጠቀም ተከታታይነት ያለው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፤

ለ) በሥልጠና ገበያ ጥናት ተለይተው በታወቁ ፍላጎቶች መሠረት ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤

(1) ሰልጣኞችን በሙያ ደረጃ፣ በእድሜ፣ በሥራ ልምድና በኢንተርፕራይዞች የስራ ዘርፍ እና የዕድገት ደረጃ በመለየት ለሥልጠና ዝግጁ ማድረግ፣

(2) የስልጠና ቦታ፣ ዘዴና ጊዜ ለይቶ መርሀ ግብር ማዘጋጀት፣

(3) በመርሀ ግብሩ መሰረት ለተመረጡ የስልጠና ርዕሶች አሰልጣኝ መመደብ፣



(4) ለስልጠና የሚያስፈልጉ ማንዋሎች፣ ሎጂስቲክስ፣ በጀትና ሌሎች የማሰልጠኛ ግብዓቶች በማሟላት ሥልጠናውን ማከናወን፤

(5) ወጥነት ያለው የስልጠና ቅደመ ዝግጅት ለማከናወን የሚዘጋጀው መርሀ ግብር የአሰልጣኝ ምደባ፣ የስልጠና ቦታ፣ ዘዴና ጊዜ ዝግጅት የሚይዛቸው ዋና ዋና ተግባራት ይሆናሉ።

## 3) የስልጠና አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ መስፈርቶች

ሀ) በሥልጠና ፍላጎት ጥናት መሰረት የተለየ፣

ለ) በግልም ሆነ በማህበር ለመሰልጠን ፍላጎት ያለውና ጥያቄውንም በማመልከቻ የሚያቀርብ፣

ሐ) ስልጠናው የሚጠይቀውን የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ያሟላ፣

መ) በሥልጠና ያገኘውን እውቀትና ክህሎት ሥራ ላይ ለማዋል ዝግጁ የሆነ፣

ሠ) በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምዘና ለመውሰድ ፍቃደኛ የሆነ

## 4) የሥልጠና አፈጻጸም

ሥልጠናዎች የኢንተርፕራይዞችን የስራ ጊዜ በማይሻማ መልኩ በዋናነት በመደበኛ የስራ ሰዓት ጊዜ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በማታ፣ በበዓልና ዕረፍት ቀናት ጨምሮ እንዲሰጥ ይደረጋል። በስልጠና አፈጻጸም የሚከተሉት ተግባራት ይከናወናሉ።

ሀ) በስልጠና መስፈርቶችና በመርሀ ግብሩ መሰረት ሰልጣኞችን መመዝገብና መደልደል፣

ለ) በተለያዩ የስልጠና ዘዴዎች ስልጠና መስጠት፣

ሐ) በስልጠናው የተገኘውን የእርካታ ደረጃ መጠይቅ በማስሞላትና ተጠቃሚዎችን በማወያየት አፈጻጸሙን መገምገም፣

መ) ሰልጣኞች የብቃት ምዘና እንዲወስዱ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣

ሠ) የስልጠና አፈፃፀም ሪፖርት ማዘጋጀት፣

ረ) ስልጠናው ያመጣውን ለውጥ በስራ ቦታ ላይ በመገኘት ውጤቱን መገምገም፤

ሸ) በስራ ላይ ላሉ ነባር ኢንተርፕራይዞች በተዘጋጀው የሙያ ደረጃ መሰረት የብቃት ማረጋገጫ ምዘና እንዲወስዱ ድጋፍና ክትትል ማድረግ።

## 5) የሥልጠና አሰጣጥ ስልት

ሀ) በዘርፉ የተሰማሩ/የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች ወደ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በማስገባት ባለባቸው የሙያ ክፍተት ላይ የተመሠረተ ተግባር ተኮር ሥልጠና እንዲሰጥ ይደረጋል፣

ለ) ስልጠናው በተቋም ውስጥ፣ በትብብር ስልጠና እና በኩባንያ ውስጥ የሚሰጥ ሲሆን መደበኛ ባልሆኑ ፕሮግራሞች በሚሰጡ የብቃት አሃዶች ላይ ያተኩራል።

ሐ) የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በግል ወይም በንግድ ማህበር ተደራጅተው ያለባቸውን የቴክኒክና የሙያ ክፍተት መሠረት



ያደረገ ሥልጠና በሥራ ቦታቸውና በክላስተር ሆነው እንዲያገኙ ይደረጋል፣

መ) የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ የተሞክሮ ልውውጥና የመልካም አሰራር መድረኮች ላይ በመገኘት ልምድ እንዲያገኙ ይደረጋል፣

ሠ) የአሰልጣኞች ሥልጠና ለሚሰጣቸው ባለሙያዎች የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉና የተግባራዊ ልምምድ መድረኮች ይመቻቻል፣

ረ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ሰልጣኞችን አሰልጥነው ከማውጣት በተጨማሪ፤-

(1) የኢንተርፕራይዞችን የእድገት ደረጃ በመለየት አቅማቸውን ገንብተው ወደ ቀጣይ ደረጃ ለመሸጋገር የሚያደርጉትን ጥረት ማገዝ፣

(2) የሙያ ብቃት ምዘናና ተከታታይነት ያለው የቴክኒክ ምክር አገልግሎት እንዲወስዱ ከከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት የጋር ዕቅድ አቅዶ መስራት፤

(3) ከሌሎች ፈጻሚ አካላት የሚገኙ ግብዓቶች በወቅቱና በሚፈለገው መጠን ቀርቦ ተልዕኮአቸውን እየተወጡ መሆኑን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

6) የቴክኒክ ሙያ /የቴክኒካል ክህሎት/ ስልጠና

የቴክኒክና ሙያ ስልጠና የሰው ኃይል፣ የገበያ ፍላጎትና የሙያ ደረጃን መሰረት ያደረገ እንደየ ኢንተርፕራይዙ የእድገት ደረጃ የሚሰጥ ስልጠና ነው።

1. ኢንዱስትሪ
   - 1.1 ጨርቃ ጨርቅና አልባሳት
     1. ሽመናና ስጋጃ ሥራ
     2. ጨርቃ ጨርቅና ስፌት
   - 1.2 የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ሥራ
   - 1.3 የብረታ ብረትና ኢንጂነሪንግ ሥራ
     1. የብረታ ብረት ሥራ
     2. የእንጨት ሥራ
     3. የቀርከሃ ሥራ
     4. የሸክላ ሥራ
     5. ጌጣ ጌጥና ዕደጥበብ ሥራዎች
     6. የኤሌክትሪክ ሥራ
     7. የጥገና አገልግሎት
   - 1.4 አግሮ ፕሮሰሲንግ

- 3.3. የባቡር መንገድ ሥራ
- 3.4. ቴሌኮሙኒኬሽን
- 3.4. ኢነርጂ(መብራት)
- 3.5. መጠጥ ውሃና መስኖ ሥራ
- 3.6. የየብስ ትራንስፖርት
- 3.7. የገጠርና አነስተኛ ትራንስፖርት

3. ማዕድን
   1. ባህላዊ የማዕድን ሥራዎች
   2. የከበሩ ድንጋዮች ልማት
4. ንግድ
   1. የማከማቻ አገልግሎት
   2. የማሸጊያ አገልግሎት
   3. የሥራ አመራር አገልግሎት
   4. ኢንተርኔትካፌ



2. የግብርና ዘርፍ (የከተማ ግብርና)
   - 2.1 ዘመናዊ የእንስሳት እርባታ፣
   - 2.2 የንብ ማነባት፣
   - 2.3 የዶሮ እርባታ፣
   - 2.4 አትክልትና ፍራፍሬ፣
   - 2.5 የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ፣
3. ኢኮኖሚ መሠረተ ልማት
   - 3.1 መንገድ ሥራ
     1. የኮብል ስቶን
     2. የገጠር መንገድ
   - 3.2 የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን
     - የግንባታ ግብአቶች ምርት
     - የስርቬይንግ ሥራ
     - ላንድስኬፒንግ
     - የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ
     - የግንባታ አገልግሎቶች

5. ባህልና ቱሪዝም
   1. ምግብ ዝግጅት
   2. ካፌና ሬስቶራንት
   3. የቱሪስት አገልግሎት
   4. የውበት ሳሎን ሥራዎች
6. ሌሎች
   1. የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች
   2. የፕሮጀክት ኢንጅነሪንግ አገልግሎት
   3. የግቢ የውበት፣ የጥበቃና ጽዳት አገልግሎት
7. ኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ
   1. የኤሌክትሮኒክስና ሶፍት ዌር ልማት

ከላይ ለተዘረዘሩት የሥራ ዘርፎች የሚሰጡት የቴክኒክ ሥልጠናዎች እንደየ ዕድገት ደረጃቸው መሠረት ያደረገ እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ወደፊት ተጠንተው የሚካተቱ የሥራ መስኮች ላይ ለተሠማሩትና ለሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የሥልጠና አገልግሎት እንዲያገኙ ይደረጋል።

### 7 የሚሰጡ የሥልጠና ዓይነቶች

በገበያ ፍላጎት ጥናት መሰረት ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ፍላጐታቸው እየተጠና ከሚከተሉት የሥልጠና አገልግሎቶች ተስማሚውን በመምረጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፡፡

1) የኢንተርፕረነርሽፕና የንግድ ሥራ ክህሎት ስልጠና

ሀ) ለጀማሪ ኢንተርፕራይዞች

(1) አደረጃጀት

(2) ንግድዎን ይጀምሩ

(3) መሰረታዊ ኢንተርፕረነርሽፕ

(4) መሰረታዊ የሒሳብ መዝገብ አያያዝ

(5) መሰረታዊ የወጪ ማስላትና ዋጋ ተመን

(6) መሰረታዊ ንብረት አያያዝ

(7) መሰረታዊ ገበያ አያያዝ

(8) የንግድ ስራ ዕቅድ አዘገጃጀት

(9) ብቃት ያለው የንግድ ሰው ማዘጋጀት (CEFE)

ለ) ለታዳጊ ኢንተርፕራይዝ

(1) ንግድዎን ያሻሽሉ፣

(2) የደንበኛ አያያዝ፣

(3) የሰው ኃይል ስራ አመራር፣

(4) የሒሳብ መዝገብ አያያዝ፣



(5) የወጪ ማስላትና ዋጋ ተመን፣

(6) መሰረታዊ የጥራትና ምርታማነት ሥራ አመራር (ካይዝን)፣

ሐ) ለበቃ ኢንተርፕራይዝ

(1) ንግድዎን ያሻሽሉ፣

(2) የደንበኛ አያያዝ፣

(3) የሰው ኃይል ስራ አመራር፣

(4) የሒሳብ መዝገብ አያያዝ፣

(5) የወጪ ማስላትና ዋጋ ተመን ፣

(6) ከፍተኛ የጥራትና ምርታማነት ሥራ አመራር(ካይዝን)፣

(7) ISO የጥራት ስራ አመራር ስርዓት፣

2) የሥልጠና አገልግሎት መረጃ አያያዝ

በየደረጃው የሚገኙ የሥልጠና አገልግሎት ሰጪ አካላት የሚከተሉትን የሥልጠና መረጃዎች መያዝ ይጠበቅባቸዋል፡፡ የተሰጡ ሥልጠናዎች ዓይነት፣ ዝርዝርና የፈጀው ጊዜ፣ በየሥልጠናዎቹ የተሳተፉ ሠልጣኞች ዝርዝር መረጃ (በተወሰዱ የሥልጠና ዓይነትና በወሰዱት ጊዜ ብዛት፣ የሰልጣኞች አድራሻ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሥራ መስክ፣ ጾታና ዕድሜ») እያንዳንዱ ሥልጠና የፈጀው አጠቃላይ ወጪ መጠንና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸውን መረጃዎች ለሚመለከታቸው አካላት በየወቅቱ መቅረብ ይኖርበታል፡፡ በዚሁ መሰረት ስልጠናው ያስገኘውን ፋይዳ በጋራ ይገመገማል፡፡

## 8. ተፈላጊና አዋጭ የቴክኖሎጂ ልማትና አቅርቦት

በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ውስጥ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ልማታችንን በብቃት መደገፍ እንዲችሉና ተወዳዳሪነታቸውን ለማሳደግ በቴክኖሎጂ አቅርቦት የታገዘ የኤክስቴንሽን አገልግሎት ሊያገኙ ይገባል።

**1) ቴክኖሎጂ መረጣ**

ሀ) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመምረጥ ሦስት መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ መስራት ለተወዳዳሪነት፣ ለገበያ ትስስርና ለኢኮኖሚ ልማት አስተዋፅኦው ወሣኝ ከመሆኑ በተጨማሪ ሀገራዊ ፋይዳውንም የጎላ እንዲሆን ያደርገዋል። እነዚህም:-

(1) የአሠራር እሴት ሰንሰለት ትንተና በመከተል በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት ላይ የዋሉና ወደ ፊት ምርታማነትን ለማሳደግ የሚውሉ ቴክኖሎጂዎችን በመለየት ማምረትና እንዳስፈላጊነቱ ማሻሻል፣

(2) ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን (ቴክኖሎጂዎችን) ደረጃ በደረጃ በአገር ውስጥ መተካትንና ለሀገር ውስጥ ገበያ ፍላጎት ማሟላት

(3) ለውጭ ምርቶች የሚውሉ ግብዓቶችን የማምረት ሂደትን የተከተለ መሆን ይኖርበታል።



ለ) ከላይ በተጠቀሱት መርሆዎች የተመረጡትን ቴክኖሎጂዎች ሙሉ ለሙሉ ወይም በከፊል በአገር ውስጥ ለማምረት/ለመተካት ቴክኖሎጂውን ከምርታማነት፣ ከምርት ጥራት፣ ከጉልበት/ኃይል አጠቃቀምና ከወጪ አንፃር አዋጭነቱን በመተንተን መምረጥ፤

ሐ) ቴክኖሎጂዎቹን በመምረጥ ሂደት ውስጥ በዋናነት የፌዴራልና የክልል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ የፌዴራልና የክልል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች/ቢሮዎች እንዲሁም የምርምርና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ሰጪ ኢንስቲትዩቶችን ማሳተፍ፤

መ) የቴክኖሎጂ መረጣ ሥራውን በተበታተነ መልክ በመሥራት የሃብት ብክነት እንዳይከሰትና የሥራ ድግግሞሽን ለማስወገድ የፌዴራል/የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲዎች በየደረጃው ያሉት የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ልማት ጽ/ቤቶች በባለቤትነት ማሳተፍ፤

ሠ) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊያገለግሉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎች ከሚከተሉት ምንጮች ሊገኙ ይችላሉ፣

(1) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣

(2) ከቴክኖሎጂ ድጋፍ ኢንስቲትዩቶች፣

(3) ከዩኒቨርሲቲዎች፣

(4) ከገጠር ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ማዕከላት፣

(5) ከአስመጪዎች፣

(6) ከከፍተኛና መካከለኛ ፋብሪካዎች፣

(7) ከነባር ኢንተርፕራይዞች፣

(8) ከድረ ገጽ (ኢንተርኔትና ከሌሎች ምንጮች) ማሰባሰብ፣

## 2) ቴክኖሎጂ ማቀብ/ማከማቸት

የማቀብ ሥራ በቴክኖሎጂ መምረጫ አቅጣጫዎችና በአዋጭነት ትንተና መሰረት የተመረጠን ቴክኖሎጂ ደረጃውን የጠበቀ ንድፍና ናሙና በማዘጋጀት ፈትሾ ለሽግግር የማብቃት ተግባር ነው። ይህ ሥራ የቴክኖሎጂውን አሰራር በነፃ የተገኙ ዲዛይኖችን የመጠቀምና ሳይንሳዊ መንገዶችን በመከተል ናሙናዎችን በታትኖና አመሳስሎ መስራትን ያጠቃልላል።

በዚህም መሰረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና እንደ ቴክኖሎጂው ውስብስብነት ደረጃ ዩኒቨርሲቲዎችና የቴክኖሎጂ ድጋፍ ኢንስቲትዩቶች

ሀ) የቴክኖሎጂውን የአሰራር ትንተና ፣

ለ) የመስሪያ ንድፍ ፣

ሐ) የአመራረት ሂደት ማንዋል ፣

መ) የቴክኖሎጂውን ናሙና በንድፉና በተገቢው ጥሬ ዕቃ የማምረት እና

ሠ) ናሙናውን ፈትሾ በማጠናቀቅ ተቋማዊ አቅም የመፍጠር ኃላፊነት ይኖርባቸዋል።



በቴክኖሎጂ ማቀብ ሥራ ዋና ተዋንያኖች የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት፣ ዩኒቨርሲቲዎች፣ ምርምርና የዘርፍ ኢንስቲቲዩቶች ሲሆኑ፣ እንደየኢንተርኘራይዞቹ የዕድገት ደረጃ የፌዴራልና የክልል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎች መረጃ በመስጠት፣ ባለሙያ በማሳተፍ የአሰራር ሂደቱን በባለቤትነት ክትትል አድርገው ግብረ መልስ የመስጠት ሃላፊነት አለባቸው።

## 3) ቴክኖሎጂ ማሸጋገር

ሀ) በቴክኖሎጂ ሽግግር፡-

(1) ቴክኖሎጂ ተጠቃሚውንና አብኘውን የመለየት፣

(2) የአብኘዎችን የብቃት ክፍተት በመለየት የማብቃት ፣

(3) ቴክኖሎጂውን በተቀመጠው ጥራት መስፈርት የማምረት፣

(4) የተመረተውን ቴክኖሎጂ ከገበያ ጋር በማስተሳሰር ወደ ተጠቃሚው የማድረስ፣

(5) የቴክኖሎጂዎቹን ፋይዳ በመዳሰስ ለቀጣይ ሥራዎች ግብረ መልስ የመስጠት ሥራዎች ይከናወናሉ፣

(6) የተረጋገጠውን ቴክኖሎጂ አቅራቢ አካላት ወጪ አተካክ ሥርዓት፣ የአብኘዎች አመራረትና የተጠቃሚዎች ትስስር፣ የአበዳሪ አካላት ዝግጅትና ፈጣን ምላሽ እንዲሁም የጥራት ቁጥጥር ሥርዓቱን በዘርፉ ፈፃሚ አካላት ቅንጅት ይፈፀማል።

(7) የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የምርት ጥራትና ምርታማነት ለማሳደግ እንዲችሉና ብቁ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ

በቴክኖሎጂ ብዜትና ሽግግር ላይ ዋና ተዋንያን በመሆን ተጨማሪ አቅም ፈጥረው የሕብረተሰቡን ችግር በዘላቂነት በመፍታትና ኋላቀር የሆኑ የማምረቻ መሣሪያዎችን በተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎች በመተካት ወደ ቀጣዩ የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ ይደረጋል።

4) ቴክኖሎጂ አብዥ ኢንተርፕራይዞች ማሟላት የሚገባቸው መስፈርቶች

በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና በምርምርና በዘርፍ ኢንስቲትዩቶች ለኢንተርፕራይዞች የተመረቱ ቴክኖሎጂዎች ዲዛይኖችንና የተረጋገጡ ናሙናዎች ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የአመራረት ሥልጠና ከተሰጣቸው በኋላ እንዲባዙና እንዲሰራጩ ይደረጋል። በዚህ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

ሀ) በሥራው መስክ በቂ ዕውቀትና ክህሎት ያለውና በቀረቡት ቴክኖሎጂዎች ላይ የአመራረት ሥልጠና የወሰደ፤

ለ) በቂ የሰለጠነ የሰው ኃይል ያለው፤

ሐ) በቂ ማሽነሪዎችና የማምረቻ መሳሪያዎች ያለው፤

መ) በቂ የማምረቻ ቦታና የጥሬ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ያለው፤

ሠ) የስራ ቦታ ደህንነትና የአካባቢ ጥበቃን መስፈርቶች ተግባራዊ ያደረገ፤



ረ) ለብዜት የተረጋገጠውን ናሙና በዲዛይኑና ስፔስፊክሽን መሠረት የሚፈለገውን ምርት በጥራት ማምረትና በተመጣጣኝ ዋጋ ማሰራጨት የሚችል፤

ሰ) እንደ አስፈላጊነቱ የተመረተውን ቴክኖሎጂ ለተጠቃሚዎች በመስሪያ ቦታቸው የመትከል ኃላፊነት የሚወስድ፤

ሸ) በመሳሪያዎቹ ላይ ለሚደርሰው ብልሽት እንደ ቴክኖሎጂው አይነት በጊዜ የተገደበ የጥገና ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት።

5) በቴክኖሎጂ ብዜትና አቅርቦት ላይ የግል ባለሀብት ተሳትፎ

ሀ) በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና በቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች የተረጋገጡ ቴክኖሎጂ ላይ ሥልጠና ከወሰዱ በኋላ አባዝተው ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በማሰራጨት፤

ለ) በሚያመርቷቸው ቴክኖሎጂዎች ላይ ለተጠቃሚዎች ሥልጠና በመስጠት፤

ሐ) ከሀገር ውጭ በተለያየ መንገድ ያገኟቸውን ቴክኖሎጂዎች በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ተመርተው ሥራ ላይ እንዲውሉ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር፤

መ) በመካከለኛና ከፍተኛ ኢንተርፕራይዞች እንዲባዙ የተመረጡ ቴክኖሎጂዎችን ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በንዑስ ተቋራጭነት በመዋዋል እንዲያመርቱ በማድረግ።

## 6) የተባዙ ቴክኖሎጂዎችን ማስተዋወቅና ሥልጠና መስጠት

ሀ) የተመረቱ ቴክኖሎጂዎችን ለሚያባዙና ለሚያሰራጩ ኢንተርፕራይዞች እንዲሁም ለተጠቃሚዎች ሥልጠና መስጠት፣

ለ) የተመረቱ ቴክኖሎጂዎችንና የፈጠራ ውጤቶችን ለሚያባዙና ለሚያሠራጩ ተቋማት እንዲሁም ለተጠቃሚዎች በንግድ ትርኢት፣ በባዛሮች፣ በማሳያ ቦታዎች፣ በፎረሞች፣ በህትመትና በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያዎች ማስተዋወቅ፣

## 7) ቴክኖሎጂ አብዥ ኢንተርፕራይዞች የሚጠቀሙባቸውን መሳሪያዎች ማግኛ አማራጮች

ሀ) ከመሣሪያ አቅራቢ ወይንም አምራች ድርጅቶች እጅ በእጅ ግዥ፣

ለ) ከአበዳሪ ተቋማት፣ ከመሣሪያ አቅራቢ ወይንም አምራች ድርጅቶች በሊዝና በኪራይ ግገር፣

ሐ) ከልማት ደጋፊ መንግሥታት በዕርዳታ፤

መ) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትና

ሠ) ከተለያዩ ኩባንያዎች የመሳሪያ አገልግሎት ግዥ ሊያገኙ ይችላሉ::



## 8) የጋራ አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት

ሀ) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚገኙ የማምረቻ መሣሪያዎች ስልጠና በማይካሄድባቸው ጊዜ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተመጣጣኝ ኪራይ እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

ለ) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያመርቷቸውን ምርቶች ጥራት ለማረጋገጥ እንዲችሉ የሚያግዝ የጥራት ማረጋገጫ አገልግሎት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እና ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ማድረግ፣

ሐ) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚያስፈልጓቸውን የላቦራቶሪ አገልግሎት ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ያገኛሉ::

## 9) የሰው ኃይል ስልጠናና የቴክኖሎጂ ልማት መረጃ

የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸው ዘርፈ ብዙ የተወዳዳሪነትና የብቃት ችግሮች መቅረፍና በስትራቴጂው ላይ እንደተቀመጠው የሰው ኃይል ስልጠናና የቴክኖሎጂ ልማት መረጃ ማግኘት የሚችሉበት የተጠናከረ የመረጃ አገልግሎት ሊሰጣቸው ይገባል:: ኢንተርፕራይዞቹ ከተለያዩና አግባብነት ካላቸው የአካባቢ፣ የሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ አካላት ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችሉ ዘንድ በየደረጃው ከሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ጋር በመገናኘት የቴክኖሎጂ፣ የጥሬ ዕቃ፣ የሥልጠናና የምክር አገልግሎት መረጃዎች በተሟላ መልክ ማግኘት ይኖርባቸዋል::

10) መረጃዎችን ከተለያዩ ምንጮች ማሰባሰብ፣ ማደራጀትና ማጠናቀር

ሀ) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ/ተቋም በየሥራ መስኩ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሊያገለግሉ የሚችሉ የተለያዩ እድገት ተኮር የስራ ዘርፎች የስልጠናና የቴክኖሎጂ መረጃዎችን ከቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩቶች፣ ከዩኒቨርሲቲዎች፣ ከፋብሪካዎች፣ከድረ ገጽ፣ ከገጠር ቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ማዕከላት፣ ከአስመጪዎች፣ ከፌዴራል አስፈጻሚ ተቋማት እና ከክልሎች ይሰበስባሉ::

ለ) ከሌሎች ምንጮች የተሰበሰቡ መረጃዎችን ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አገልግሎት ሊውሉ በሚችሉበት መልክ በመለየት፣ በማደራጀትና በማጠናቀር ለተለዩት የስራ ዘርፎች የማምረቻ መሳሪያዎች ዝርዝር መግለጫ፣ የጥሬ ዕቃ፣ የቴክኖሎጂ ልማት፣ የገቢና ኤክስፖርት ምርቶች፣ የግብዓቶችና የኢንተርፕራይዞች ብቃትና ጥራት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎች መቅረብ ይኖርባቸዋል::

11) መረጃዎችን ማሰራጨት

የተጠናቀረው መረጃ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በቀላሉ ሊያገኙት በሚችሉበት አማራጮች በዋናነት በካታሎግ፣ በመጽሔት፣ በብሮሸር፣ ድህረ ገጽና በሲዲ በማዘጋጀት በየደረጃው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ/ ተቋም፣ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ በአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ ውስጥ ለተጠቃሚዎች እንዲቀርብ ይደረጋል:: በየደረጃው የሚገኙ አስፈጻሚ አካላት ወቅታዊና በጊዜ መድረስ ያለባቸውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት መረጃዎች እንዳስፈላጊነቱ ለሬዲዮና ለቴሌቪዥን ድርጅት በመላክ በአየር ላይ መዋሉን ክትትል ማድረግ አለበት::



9. የጥራትና ምርታማነት /ካይዘን/ አገልግሎት

የጥራትና ምርታማነት/ካይዘን/ አገልግሎት የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ብክነትን በመቀነስ በሥራቸው ትርፋማ እንዳይሆኑ መሰናክል የሆኑባቸውን የአመራርና አሰራር ችግሮችን ለመፍታት የሚሰጥ ድጋፍ ነው::

በዕድገት ተኮር የሥራ ዘርፍ የተሰማሩ ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንደየእድገት ደረጃቸው የንግድ ሥራቸውን ለማሳደግ እና ብክነትን በመቀነስ የሚያመርቱት ምርት በገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን ለማድረግ የጥራትና ምርታማነት/ካይዘን/ አገልግሎት ከፍተኛ ሚና አለው::

1) በካይዘን አገልግሎት ውስጥ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

ሀ) ስለካይዘን አገልግሎት አስፈላጊነት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ መሥራት፣

ለ) የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸውን ውስጣዊና ውጫዊ ችግሮች በመለየትና ላጋጠሟቸው ችግሮች ተጨባጭ መፍትሔ በመስጠት ኢንተርፕራይዞቹን ተወዳዳሪ ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የማማከር አገልግሎት እና ተግባር ተኮር ስልጠና እንዲሰጥ ማድረግ፣

2) የጥራትና ምርታማነት ድጋፍ ተጠቃሚዎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርት

ሀ) የድጋፍ ተጠቃሚ ለመሆን በራስ ተነሳሽነት ጥያቄ ማቅረብ፣

ለ) ለድጋፍ አስፈላጊ የሆኑ ተአማኒነት ያላቸው መረጃዎችን ለመስጠት ዝግጁ የሆነ፣

ሐ) ከአሰልጣኝ የሚሰጠውን የሥራ ድርሻ ለመተግበር ዝግጁና ፍቃደኛ የሆነ፣

መ) የድጋፍ አገልግሎት ጥቅም በአግባቡ የተረዳ ፣

ሠ) በተሰማራበት ወይም ሊሰማራ ባሰበበት የሥራ መስክ በልምድ ወይም በትምህርት የተገኘ ተጨበጭ ክህሎትና እውቀት ያለው መሆን አለበት፣

3) የምክር አገልግሎት አፈጻጸም ሂደት ደረጃዎች

ሀ) በመስኩ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በተለያየ ዘዴዎች በመጠቀም ስለ አገልግሎቱ ጠቀሜታ ግንዛቤ መፍጠርና ማነሳሳት /Sensitization and Stimulation/፣

ለ) የካይዘን አገልግሎት ተጠቃሚዎችን መመልመል፣

ሐ) ለካይዘን አገልግሎት የተመለመሉ የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መረጃ በመሰብሰብ የነባራዊ ሁኔታ ግምገማ /Situational Analysis/ ማድረግ፣

መ) የነባራዊ ሁኔታ ትንተና መነሻ በማድረግ ለተቋሙ ችግር አማራጭ መፍትሄዎችን ማስቀመጥ፣ በአማራጭ መፍትሔዎቹ ላይ በመወያየት፣ ለችግሩ የተሻለ መፍትሔ የሚሆነውን መምረጥ፣



ሠ) የተመረጠውን የመፍትሔ ሃሳብ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል የድርጊት መርሃ-ግብር (Action Plan) ማውጣት፣

ረ) የካይዘን አገልግሎት ተጠቃሚውና አገልግሎት አቅራቢው የውል ስምምነት መፈራረም፣

ሰ) በድርጊት መርሃ-ግብሩ መሠረት የተግባር እንቅስቃሴ ለማድረግ የተቋሙ የግል የክትትል ፋይል ወይም ቋሚ መዝገብ ማዘጋጀት

ሸ) በድርጊት መርሃ ግብሩ መሠረት ተገቢውን ድጋፍ ማግኘቱን ማረጋገጥ፣

ቀ) ተቋሙ ምክርና የካይዘን አገልግሎት በማግኘቱ ያመጣውን ለውጥ መገምገምና ተገቢውን ግብረ መልስ ማድረግ፣

በ) አገልግሎቱ ቅድሚያ ትኩረት በሚሰጣቸው እድገት ተኮር የሥራ መስኮች ላይ የእሴት ሰንሰለት ትንተና መሠረት በማድረግ ይበልጥ ያተኮረ ይሆናል።

10. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች የሚሰጡ ሥልጠናዎች

1) በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ እና የከተማ ልማት ፖሊሲ፣
2) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ፣
3) ስለጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት የአንድ ማዕከል አገልግሎት ሥርዓት፣
4) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት አገልግሎትና ድጋፍ አሰጣጥ የአፈፃጸም መመሪያዎች፣

5) የካይዘን አገልግሎት አሰጣጥ
6) የንግድ ልማት አገልግሎት በሚሸፍናቸው ዋና ዋና መስኮች (በገበያ፣ በብድርና ቁጠባ፣ በሂሣብ አያያዝ፣ በንግድ ዕቅድ ዝግጅት፣ በመረጃ፣ በማህበር አደረጃጀትና አመራር በኢንተርፕርነርሽፕ)፣
7) የእሴት ሰንሰለት ልማት፣ የክላስተር ልማት፤
8) በማኅበረሰብ ልማት (Community Development) እና በህብረተሰብ አገልግሎት (Social Work)፣
9) የካይዘን ወይም ከቴክኒክ ሥራ ጋር በተያያዘ እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ፓኬጆች /ቴክኒካል ክህሎት ድጋፍ፣ ቴክኖሎጂ ድጋፍ ኢንተርፕሩነርሽፕ እና ንግድ ክህሎት ድጋፍ እና ጥራትና ምርታመነት ወይም ካይዘን/ ላይ ስለ ጥራት አጠባበቅ፣ ስለጥሬ ዕቃ አያያዝና አጠቃቀም፣ ስለ ነባርና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና መሳሪያዎች አጠቃቀም፤
10) ሌሎች ከስራዉ ጋር አግባብነት ያላቸዉን ወቅታዊ ሥልጠናዎች መስጠት።

## 11. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች /የአሰልጣኞች/ ዋነኛ የሥራ ድርሻ

1) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ያሉባቸውን የኢንተርፕርነርሺፕ፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የፋይናንስ፣ የገበያ ችግሮች ለማቃለል ሁሉ አቀፍ የምክር አገልግሎት ድጋፍ መስጠት፤
2) በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ፣ የምክር አገልግሎት እንዲሁም በአገልግሎቱ ተጠቃሚነት ላይ ግንዛቤና የማነሳሳት ስራ መስራት፤



3) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ መረጃዎች፣ የፋይል አደረጃጀት ስልት ለእያንዳንዱ ድጋፍ ተቀባይ ኢንተርፕራይዝ ወይም ግለሰብ የነባራዊ ሁኔታ ትንተና (situation analysis) ፎርማቶች በመጠቀም በተገቢው ማደራጀት፤
4) ከአገልግሎት ተቀባዩ ጋር የተግባር መርሃ- ግብር (Action planning) ማዘጋጀት፤
5) በድርጊት መርሃ ግብሩ መሠረት ኢንተርፕራይዙ ተገቢውን ድጋፍ ማግኘቱን ማረጋገጥ እና የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን የተሰጠበትን ሪፖርት ማዘጋጀት፣ የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ዝርዝር መረጃ ለዚሁ አላማ በተዘጋጀዉ መዝገብ/Journal/ ላይ መመዝገብ፣
6) ኢንተርፕራይዞቹ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በማግኘታቸው ያመጡት ለውጥ በተከታታይ መገምገም፣ ችግሮችም ማስተካከል፣
7) ለኢንተርፕራይዞች የተሰጡት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ በሙያ ብቃት ምዘና ማረጋገጥ:
8) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አሰልጣኝ ከላይ በዝርዝር የተቀመጡትን ተግባራት ባይፈጽም ሙሉ ተጠያቂ ይሆናል።

## 12. የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ፋሲሊቴተር የሥራ ድርሻ

1) የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከመረጃ፣ ከሥልጠናና ምክር አገልግሎት፣ ከኢንተርፕርነርሺፕ፣ ከሂሳብ አያያዝ፣ ከቴክኖሎጂና ማምረቻ መሣሪያ አኳያ ያሉባቸውን መሠረታዊ ችግሮች በዝርዝር መለየት፤

2) ለተለዩ ችግሮች የሚመለከታቸውን አካላት ድጋፍ እንዲሰጡ የተደራጀ መረጃ ማስተላለፍ፣

3) የተለዩ ችግሮች በዘርፉ አስፈፃሚ አካላት መፍትሄ ማግኘታቸውን መከታተልና ለአንድ ማዕከል ሪፖርት ማድረግ፤

4) ከተለያዩ የግል፣ የመንግስት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ባለድርሻዎችና ተባባሪዎች ጋር የሥራ ትብብር (የጋራ መግባቢያ ሰነድ) የሚፈፀምበት ሁኔታ ያመቻቻል፤

5) ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ ሁኔታዎች ችግር ሲያጋጥማቸው አስቀድሞ ከተለዩትና የሥራ ትብብር የውል ስምምነት ከተገባባቸው ተቋማትና ከሌሎችም አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር የማገናኘት ሥራ መስራት፣

6) የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አመቻች ከላይ በዝርዝር የተቀመጡት ተግባራት ባይፈጽም ሙሉ ተጠያቂ ይሆናል።

## 13.የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ዘዴ

1) በግል ወይም በንግድ ማህበር ለተደራጁ ኢንተርፕራይዞች በሥራ ቦታ በመገኘት ወይም ጉብኝት በማድረግ የንግድ ልማት ምክር አገልግሎት መስጠት፣

2) በተመሳሳይ የሥራ መስክ ተሰማርተው የሚገኙ ኢንተርፕራይዞች በልማት ቡድን በማደራጀት በሥራ ቦታቸው በአካል በመገኘት ወይም በክላስተር ማዕከል መደበኛ የንግድ ምክር አገልግሎት መስጠት፣



## 14.የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ተጠቃሚዎች አመላመል

1) የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በራሳቸው ተነሳሽነት በቀጥታ በሚያቀርቡት ማመልከቻ፣

2) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ በጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የስራ ቦታ በአካል ተገኝተው በሚያደርጉት የፍላጎት ግምገማ ሪፖርት፣

3) የልማት ሰራዊት አደረጃጀት፣ የዘርፍ ማህበራት፣ የዘርፍና የንግድ ምክር ቤቶች፣ የሙያ ማህበራት እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው አካላት ለአባሎቻቸው እንዲሰጥላቸው መልምለው በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት።

## 15. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የወጪ አሸፋፈን

ጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞቹ የሚያገኟቸውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ጥቅም በዝርዝር እንዲረዱ በማድረግ በማንኛውም ደረጃ ያሉት ኢንተርፕራይዞች ወጪ ከመጋራት ነጻ ሆነው ወጪው በቴክኒክና ሞያ ማሰልጠኛ ተቋማት፣ በከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ/ቢሮ ወይም በሌላ አካል የሚሸፈንበት ሁኔታ ተመቻችቶ ድጋፍ ይሰጣቸዋል።

## 16. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ መስጫ ጊዜና ፕሮግራም

1) አንድ አሰልጣኝ ሃምሳ በመቶ /50%/ የስራ ጊዜውን የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ይሰጣል።

2) አገልግሎት የሚሰጠው አሰልጣኝና ተጠቃሚ ኢንተርፕራይዝ በጋራ የተስማሙበት በቀናት የተከፋፈለ ሳምንታዊ የሥራ ፕሮግራም /Weekly Work Schedule/ ይኖረዋል፤

3) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጠው የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ተከታታይና ቀጣይነት ያለው በድርጊት መርሃ ግብሩ መሠረት የሚከናወን መሆን አለበት፤

4) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ዓመታዊ፣ የግማሽ ዓመት፣ የሩብ ዓመት እና ወርሃዊ ዕቅድ ይኖራል፤

## 17. የግብይት ማበልጸጊያ ድጋፍ

1) ኢንተርፕራይዞችን የተለያዩ የገበያ ትስስር ዘዴዎችን እንዲያውቁ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናና የምክር አገልግሎት መስጠት፤

2) ለኢንተርፕራይዞች የንዑስ ተቋራጭነት፣ የአውትሶርሲንግ፣ የፍሬንቻይዚንግ እና የአውትግሮወር የገበያ ትስስር ስልቶችና አጠቃቀማቸው ላይ የተግባር ድጋፍ ማድረግ፤

3) ኢንተርፕራይዞች ጨረታ በሚወዳደሩበት ወቅት የጨረታ ሰነድ ዝግጅት ላይ ድጋፍ ማድረግና የጨረታ አፈጻጸሙ ላይ ክትትል ማድረግ፤

4) ኢንተርፕራይዞች በተለያዩ የገበያ ትስስር ያገኟቸውን ገበያዎች በብቃትና በጥራት እንዲወጡ ሙያዊ ድጋፍ በመስጠት ማብቃት፤

5) ኢንተርፕራይዞች በአካባቢያቸው ከሚገኙት አነስተኛና መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር በምርት ግብአት አቅርቦትና በከፊል ምርት ማምረት ትስስር እንዲኖር ድጋፍ መስጠት፤



## 18. ምርጥ ተሞክሮዎችን መቀመርና ማስፋት

በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የላቀ ውጤት ያመጡ ኢንተርፕራይዞችን ውጤታማ እንዲሆኑ ያስቻላቸውን የዕቅድ፣ የአፈፃፀምና የአሠራር ልምድ በማደራጀትና በመቀመር ምርጥ ተሞክሮዎችን በመለየት በስልጠና፣ በልምድ ልውውጥና በንግድ ልማት ምክርና በካይዘን አገልግሎት ወደ ሌሎች ኢንተርፕራይዞች በማሸጋገር የተሳካ ውጤት እንዲያመጡ በቅርበት ክትትል እና ድጋፍ ይደረጋል፡፡

### 1) የምርጥ ተሞክሮ መቀመሪያ መስፈርቶች (ቼክ-ሊስት)

ሀ) ሞዴል ኢንተርፕራይዙ ያሉበትን ችግሮች በራሱና በሚሰጠው ድጋፍ የፈታበት አግባብ እንዴት መለየት እንደቻለ፤

ለ) የተለዩ ችግሮችን ለመፍታት የተደረገለት የማምረቻ መሣሪያ፣ የንግድ ልማትና ካይዘን አገልግሎት፣ የቴክኖሎጂ ልማትና ስልጠና ድጋፍ በውጤታማ መንገድ እንዴት እንደተጠቀመ፤

ሐ) እንዴት ልማታዊ አስተሳሰብ ሊያሳድግ እንደቻለ፤

መ) የሥራ ክህሎት አጠቃቀም፤

ሠ) በገበያ ውስጥ በምርት ጥራትና በዋጋ እንዴት ተወዳዳሪ መሆን እንደቻለ፤

ረ) በገበያ የሚፈለገው የምርት ጥራትና ስታንዳርድ እንዴት ሊጠበቅ እንደቻለ፣

ሰ) እንዴት ውጤታማ ተቋማዊ አመራርና አደረጃጀት በስራ ላይ እንዳዋለ፣

ሸ) ምርታማነቱን እንዴት እንዳሳደገ፣

ቀ) የሚሰጡ መንግስታዊ ድጋፎችንና አገልግሎቶችን በአግባቡ መጠቀም እንዴት እንደቻለ /ብድር፣ ማምረቻ ቦታ፣ ገበያ/፤

በ) ያለውን የገበያ ድርሻ እንዴት እንዳሳደገ፣

ተ) ለተከታታይ ዓመታት እንዴት ትርፋማ መሆን እንደቻለ፣

ቸ) ካፒታል እንዴት እንዳሳደገ፣

ኀ) ለሌሎች የስራ ዕድል መፍጠር እንዴት እንደቻለ፣

ነ) በኢንተርፕራይዙም ሆነ በተቀጣሪ ሠራተኞች ዘንድ እንዴት ቁጠባን ሊያሳድግ እንደቻለ ያካተተ ይሆናል፡፡

2) የምርጥ ተሞክሮ መቀመሪያ ሰነድ ማዘጋጀት

ሀ) የተሰበሰበው መረጃ መተንተን፤

ለ) ዋና ዋና የሚስፋፉ ምርጥ ተሞክሮዎችን መለየት፤

ሐ) ለሽግግር በሚያመች መልክ ሰነዱን ማዘጋጀት፤

3) ምርጥ ተሞክሮዎችን የማስፊያ ስልት

ሀ) በየደረጃው ኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ባለሙያ እና ፋሲሊቴተሩ በጋራ የተሻለ ምርታማነትና ጥራት ያላቸውን ኢንተርፕራይዞች



እንደየእድገት ደረጃቸው ለሌሎች ኢንተርፕራይዞች ልምዳቸውን የሚያካፍሉበት መድረክ በማዘጋጀት፣

ለ) ከውጪና ከሀገር ውስጥ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በመቀመር በኤክስቴንሽን አገልግሎት ለኢንተርፕራይዞች በማሸጋገር፡፡

## 19. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች

### 1) የሰው ኃይል

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ሥራ መረጃ የማደራጀት፣ የሰው ኃይል ልማትን፣ የቴክኖሎጂ መረጣና አቅርቦት፣ የግብይት ማበልጸጊያ፣ የሂሳብ መዝገብ ዝርጋታ፣ የኢንተርፕርነርሽፕና የንግድ ሥራ ክህሎት እና የካይዘን ተግባራትን ያካተተ በመሆኑ በየደረጃው የሚደራጀው መዋቅር እንደአስፈላጊነቱ ተግባሩን በብቃት ለማከናወን እንዲችል እንደየ ኢንተርፕራይዞቹ እድገት ደረጃ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መመዘኛዎች መሰረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞች አገልግሎቱን ይሰጣሉ፡፡

ሀ) ከኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ጋር አግባብነት ያለው የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ ያላቸው፣

ለ) በቴክኒክና ሙያ ትምህርቱና ስልጠና ስትራቴጂ፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ስትራቴጂ እና የአገልግሎት የአፈጻጸም ስርዓት ላይ ስልጠና ያገኙና በቂ ግንዛቤ ያላቸው፣

ሐ) በንግድ ልማትና በካይዘን አገልግሎት ሥልጠና ያገኙ፣

መ) የንግድ ልማት አገልግሎት በሚያካትታቸው መስኮች (በግብይት ስርዓት፣ በፋይናንስ ድጋፍ፣ በኢንተርፕርነርሽፕ፣ የሂሳብ አያያዝ ዝርጋታ፣ በመረጃ፣ በንግድ ዕቅድ ዝግጅት፣ በቴክኖሎጂ ልማት) ስልጠና ያገኙ፣

ሠ) በዘርፉ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውን ጥረት ለመደገፍ ጠንካራ ተነሳሽነትና ጥሩ ስነ- ምግባር ያላቸው፣

2) ቁሳዊ ግብዓቶች

በየደረጃው የሚሰጡትን አገልግሎቶች በተሟላ አኳኋን ለማቅረብ ለሥራው ተፈላጊ ቁሳዊ ግብዓቶች ሊሟሉ ይገባል በመሆኑም፣

ሀ. የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ቀጣይነት ያለው እንዲሆንና የጥራትና ምርታማነት ማሻሻያ ሥራ አመራር (KAIZEN) እና ለመረጃ አያያዝና ስርጭት አገልግሎት የሚያስፈልጉ ቁሳዊ ግብዓቶች መሟላት ይኖርበታል፡፡

ለ. ለሰው ኃይል ሥልጠናና ለቴክኖሎጂ አቅርቦት ድጋፎች የሚውሉ ወርክሾፖች እንደሙያ ዘርፉ በተሟላ የማሰልጠኛና ማምረቻ መሣሪያዎች፣ ማሽነሪዎችና መገልገያዎች እንዲደራጁና እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

ሐ. ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ ለሚወጡ አሰልጣኞች የትራንስፖርት አማራጮችን ማመቻቸት፡፡



3) የፋይናንስ አቅርቦት

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በብቃትና በጥራት ለመስጠት እንዲቻል በየደረጃው የሚገኙ ፈጻሚ አካላት አስፈላጊውን በጀት ዕቅድ በመያዝ ደረጃ በደረጃ ለኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ግብዓቶች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የፈጻሚና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 20. የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1) ውጤታማ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓት እንዲዘረጋ ይደግፋል ያስተባብራል

2) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጡ ላይ ሚና ያላቸውን የፈጻሚ ተቋማት አቅም ይገነባል

3) ተለይተው የሚቀርቡ ችግሮችን ለዘርፉ ም/ቤት ጉባኤ ቀርበው የመፍትሄ አቅጣጫዎች እንዲቀመጥላቸው ያስተባብራል

### 21. የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ ና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

1) የፌደራል ከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋሉ ችግሮችን ሊፈታ የሚችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል ያስተባብራል

ለ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የክልል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲዎችን በመደገፍ የመፈፀም እና የማስፈጸም አቅማቸውን ያሳድጋል ፤

ሐ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት በመጠቀም የተለወጡ ኢንተርፕራይዞችን ተሞክሮ የመቀመርና የማስፋት ስራውን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል

መ) ከኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ጋር በተያያዘ የዘርፉን ልማት የሚያፋጥኑ ተሞክሮዎችን ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር የመቀመርና የማስፋት ስራውን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል

ሠ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ እና በወቅቱ እንዲሰባሰቡ፣ ተደራጅተውና ተተንትነው ጥቅም ላይ እንዲውሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

ረ) በየሩብ አመቱ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ኤጀንሲ ጋር በመቀናጀት ለክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች የአካል ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

ሰ) በየስድስት ወሩ የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አፈጻጸም በዘርፉ ም/ቤት ተገምግሞ ለሚለዩ ችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ክትትል እና ድጋፍ ያደርጋል



## 2) የክልል ከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አመቻቾችን እና ኤጀንቶችን አቅም ያጎለብታል፣

ለ) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

ሐ) ኢንተርፕራይዞች የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማስገንዘብ፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፣ ይደግፋል፣ ያስባብራል

መ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎች በአግባቡ እንዲሰበሰቡና እንዲደራጁ ይደግፋል ፣ ይከታታላል ያስተባብራል

ሠ) በአንድ ማዕከል አገልግሎት የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግትሎት አገናኝ ባለሙያ የቴ/ሙ/ት/ስልጠና ተቋማት እንዲመድቡ ያስተባብራል

ረ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ የተለወጡ ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲቀመር እና እንዲሰፋ ይደግፋል፣ ይከታታላል፣ ያስተባብራል

3) የዞን/ክፍለ ከተማ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት

ሀ) ስለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለኢንተርፕራይዞች፣ አስፈጻሚ አካላትና ሠራተኞች ግንዛቤ ማስጨበጥ፣ የማስተዋወቅና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ይሰራል፣

ለ) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል

ሐ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ማጠናቀር፣ ሪፖርት ማዘጋጀትና ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

መ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ የተሰወጡ ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲቀመር እና እንዲሰፋ ይደግፋል፣ ይከታታላል ያስተባብራል

4) የከተማ/ወረዳ የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤት ሚና

ሀ) ስለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ለኢንተርፕራይዞች፣ አስፈጻሚ አካላትና ሠራተኞች ግንዛቤ ያስጨብጣል፣ የማስተዋወቅና የሕዝብ ግንኙነት ስራ ይሰራል፣

ለ) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት እንዲሟሉ ያስተባብራል



ሐ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና ሪፖርት ማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

መ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ የተሰወጡ ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲቀመር እና እንዲሰፋ ያደርጋል

ሠ) ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ጋር በመቀናጀት የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆን ያደርጋል፣

ረ) በሥራው የተሻለ ብቃት ያላቸውንና ውጤት ያስመዘገቡ ሠራተኞችን ያበረታታል።

5) የአንድ ማዕከል አገልግሎት መስጫ ጣቢያ

ሀ) ስለኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አስፈላጊነት እና ጠቀሜታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ይሰራል

ለ) የአገልግሎቱ ተጠቃሚዎችን በመስፈርቱ ይመለምላል፣

ሐ) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽ አገልግሎት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን በተሟላ ደረጃ ያደራጃል፣ ለተጠቃሚዎች ያሰራጫል።

መ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ድጋፍ የሚፈቱትን ችግሮች ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ያስተላልፋል፣

ሠ) በየወቅቱ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት የሚሰጡ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቶች ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ሪፖርት ይቀበላል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላለፋል።

ረ) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎቱ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት በማገናኘት አብሮ የሚሰራ የኢንዱስትሪ አክስቴንሽን አገልግሎት አመቻቾች እንዲመደቡ ያደርጋል፣

## 22.የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

1) የፌዴራል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት

ሀ) የክልል ቴ/ሙ/ት/ስልጠና ኤንሲዎችን/ቢሮዎችን/ተቋማትን አቅም ይገነባል፣

ለ) ለኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች በየደረጃው እንዲሟሉ ይደግፋል ፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል

ሐ) ለተለዩ ሙያዎች የሙያ ደረጃ ምደባና የብቃት ምዘና መሳሪያዎች እንዲዘጋጁ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል

መ) ሀገራዊ ፋይዳቸው የጎላና የናሙና ወጪያቸው ከፍተኛ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የመለየት፣ የማከማቸትና የማሸጋገር ሂደቶችን በመሪነት ያከናውናል፣

ሠ) የቴክኖሎጂ ልማት ስራን በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊረዱ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣



ረ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሞክሮ መቅሰሚያ ትምህርታዊ ስልጠናዎችና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን ያመቻቻል፣ ያስተባብራል

ሰ) በየሩብ አመቱ ከፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አፈጻጸም መገምገምና ለችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ያስተባብራል

ሸ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና፣ ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

ቀ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ የተለወጡ ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲቀመር እና እንዲሰፋ ይደግፋል፣ ይከታታላል ያስተባብራል

በ) ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት መምህራን የክህሎት ክፍተታቸውን በማጥናት ተጨማሪ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ተ) በሥሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ለኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራ አመራርና የቴክኒክ ስልጠና ብቃታቸው በተረጋገጠ ባለሙያዎች እንዲሰጥ ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

**2) የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ/ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) በክልሉ ውስጥ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን አቅም ይገነባል፣ለ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጉ ግብዓቶች (የሰው ሀይል፣ ቁሳዊና ፋይናንስ) በየደረጃው እንዲሟሉ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል

ሐ) ለተለዩ ሙያዎች የሙያ ደረጃ ምደባና የብቃት ምዘና መሳሪያዎች እንዲዘጋጁ እና ተግባራዊ እንዲሆኑ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል፣

መ) ሀገራዊ ፋይዳቸው የጎላና የናሙና ወጪያቸው ከፍተኛ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን የመለየት፣ የማከማቸትና የማሸጋገር ስራዎችን ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ያስተባብራል

ሠ) የቴክኖሎጂ ልማት ስራን በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊረዱ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣

ረ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሞክሮ መቅሰሚያ ትምህርታዊ ስልጠናዎችና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን ያመቻቻል፣ ያስተባብራል፣

ሰ) በየሩብ አመቱ ከፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አፈጻጸም መገምገምና ለችግሮች የመፍትሄ አቅጣጫ እንዲቀመጥ ያስተባብራል፣



ሸ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

ቀ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ የተለወጡ ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲቀመር እና እንዲሰፋ ይደግፋል፣ ይከታታላል ያስተባብራል

በ) ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት አሰልጣኞች የክህሎት ክፍተታቸውን በማጥናት ተጨማሪ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ተ) በሥሩ የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ተቋማት ለኢንተርፕራይዞች የንግድ ስራ አመራርና የቴክኒክ ስልጠና ብቃታቸው በተረጋገጠ ባለሙያዎች እንዲሰጥ ያስተባብራል፣ይመራል፣ ድጋፍና ክትትል ያደርጋል።

**3) የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) የተሟላና ለውጤታማነት የሚያበቃ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ይሰጣል፤

ለ) አዋጭ ቴክኖሎጂዎች በመተንተን መምረጥ፣ የዲዛይንና ናሙና ማዘጋጀትና ፈትሾ በማረጋገጥ ለአብዥዎች ስልጠና በመስጠት ያሰራጫል፣

ሐ) ለሰው ሃይል ልማት፣ ለቴክኖሎጂ አቅርቦትና ለኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት ስልጠና ማንዋል ያዘጋጃል

መ) ተለይተውና ተመልምለው የቀረቡላቸውን ሰልጣኞች በተዘጋጀው የስልጠና ማንዋል መሰረት ስልጠና በመስጠት ስልጠናውን በተገቢው ሁኔታ ላጠናቀቁ የስልጠና ማጠናቀቂያ ማስረጃ ይሰጣል፣

ሠ) ልዩ ፍላጎት ላላቸውና ለሞዴል ኢንተርፕራይዞች ልዩ የሥልጠናና ምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

ረ) በኢንተርፕራይዞች የዕድገት ደረጃ መሠረት ተፈላጊ፣ ጥልቀትና ስፋት ያለው ለተወዳዳሪነት የሚያበቃ የኩባንያ ውስጥ ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት ይሰጣል፣

ሰ) ሠልጣኞች ለሙያ ብቃት ምዘና እንዲዘጋጁ ድጋፍ ይሰጣል፣

ሸ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ መረጃዎችን በተዘጋጁ ፎርማቶች በመጠቀም በተገቢው ማደራጀት፣ የነባራዊ ሁኔታ ትንተና (Situation Analysis) የተግባር መርሀ -ግብር (Action Planning) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን ድጋፍ የተሰጠበት ሪፖርት (Report on IES Delivery) ያዘጋጃል፣

ቀ) የመሳሪያ ኪራይ አገልግሎት መስጠትና የመለዋወጫ ዕቃዎችን በመሥራት በአካባቢያቸው ለሚገኙ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ ያደርጋል፣

በ) በቴክኖሎጂ አመራረት ሂደት፣ በምርት ጥራትና ምርታማነት፣ በዲዛይን፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችየሥራ ላይ ስልጠናና ምክር አገልግሎት ይሰጣል፣

ተ) ለንግድ ስራ አመራርና ለቴክኒክ ስልጠና አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች (የሠው ሐይል፣ የፋይናንስ፣ የማሰልጠኛ መሣሪያዎች) መሟላታቸውን በማረጋገጥ ገበያ መር ሥልጠና ይሰጣል፣



ቸ) ለጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከማምረቻ መሳሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች ጋር በተያያዘ ያሉባቸውን ችግሮችና ክፍተቶች በተመለከተ ዝርዝር ጥናት ያደርጋል፣

ኀ) የቴክኖሎጂ ልማት ስራን በዓይነት ወይም በገንዘብ ሊረዱ የሚችሉ ሀገር በቀልና ዓለም አቀፍ ድጋፍ ሰጪ ድርጅቶች እገዛና ድጋፍ እንዲያደርጉ ያስተባብራል፣

ነ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የተሞክሮ መቅሰሚያ ትምህርታዊ ስልጠናዎችና የልምድ ልውውጥ ፕሮግራሞችን በማመቻቸት የተቋሙን አቅም ይገነባል

ኘ) በየወሩ ከፈጻሚ አካላት ጋር በመሆን የኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን አገልግሎት አፈጻጸም መገምገምና ለችግሮች የመፍትሄ እቅጣጫ እንዲቀመጥ ያደርጋል :

አ) የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን የሚመለከቱ መረጃዎችን በማሰባሰብ፣ በማጠናቀርና ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያስተላልፋል፣

ከ) በኢንዱስትሪ ኤክስቴሽን ድጋፍ የተለወጡ ኢንተርፕራይዞች ተሞክሮ እንዲቀመር እና እንዲሰፋ ይደግፋል፣ ይከታታላል ያስተባብራል

ኸ) የተቋሙ አሰልጣኞች የክህሎት ክፍተታቸውን በማጥናት ተጨማሪ ስልጠና የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

**4) የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት**

ሀ) ለኢንተርፕራይዞች ጠቀሜታ ያላቸውን ተፈላጊና አዋጭ ቴክኖሎጂዎችን በጥናትና በምርምር በመፍጠር ያስተዋውቃል፣

ለ) ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎች በአካባቢና በቀላል ጥሬ ዕቃ እንዲመረቱ የሚያስችል ጥናትና ምርምር በማድረግ ውጤቱን ለተለያዩ ተቋማት ያስተዋውቃል፣

ሐ) በተመረጡ ቴክኖሎጂዎች አጠቃቀምና አመራረት ዙሪያ ለኢንተርፕራይዞች ስልጠና፣ የምክር አገልግሎት እና አስፈላጊ መረጃዎች ይሰጣል።

መ) የኢንተርፕርነርሽፕ ማስተባበሪያ ማዕከላትን በማቋቋም ለተማሪዎች እና ለሌሎች ማህበረሰብ ተከታታይነት ያለው የኢንተርፕርነርሽፕ ስልጠና ይሰጣል



# ክፍል አምስት

## ክትትል፣ ድጋፍ፣ ግብረ መልስ እና ማበረታቻ ስርዓት

### 23. ክትትልና ድጋፍ

1) የፌዴራልና የክልል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ/ቢሮ እና የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በጋራ በመሆን ዓመታዊ ዕቅዳቸውን በማዘጋጀት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትን በጥሬ ዕቃ፣ በማሽን አቅርቦትና በአሰልጣኞች ምደባ በተሟላ ሁኔታ በማደራጀት ለነባርና አዳዲስ ኢንተርፕራይዞች ስልጠና በመስጠትና በየጊዜው አቅማቸውን በመገምገም ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል፣

2) በሀገር አቀፍ ደረጃ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ እና የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በመቀናጀት በአመት አራት ጊዜ በጋራ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

3) በክልል ደረጃ የክልሉ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና እና የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በመቀናጀት በአመት አራት ጊዜ በጋራ በክልል በሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በአካል በመገኘት ክትትልና ድጋፍ ማድረግ አለባቸው።

4) በተጨማሪ በክልሎች በሚወጣው የአስፈጻሚዎች የጋራና የተናጠል የክትትልና ድጋፍ መርሀ ግብር መሰረት የሚፈጸም ይሆናል።

## 24. ግብረ-መልስ

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በተቀናጀና በተሳካ መልክ ለመምራት ከላይ በተቀመጠው የክትትልና ድጋፍ ስርዓት መሰረት በየደረጃው የሚገኙ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት እና የዘርፉ ልማት አስፈጻሚ አካላት በቅንጀት ግብረ መልሱን በማደራጀት ለሚመለከታቸው ፈጻሚዎች በማድረስ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 25. የማበረታቻ ሥርዓት

የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን አገልግሎትን በሚፈለገውና ውጤታማ በሆነ መንገድ ተግባራዊ ያደረገና ተጨባጭ ለውጥ ያስመዘገበ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋም እና የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ጽ/ቤትና ጉልህ አስተዋዕዖ ላደረጉ የኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ማበረታቻ የሚያገኙ ሲሆን ማበረታቻውም 60% ለተቋሙ ወይም ለጽ/ቤቱ እና 40% ለአሰልጣኙ ወይም ለባለሙያው የሚደርስ ድርሻ ይሆናል፡፡ ይህን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልግ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ በፌዴራል የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲ እና የከተማ የስራ ዕድል ፈጠራ እና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በጋራ ይዘጋጃል፡፡



# ክፍል ስድስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 26.መመሪያ ስለማሻሻል

ይህ ሞዴል መመሪያ የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ለማሳደግ እንዲሁም ከአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገት ጋር ለማጣጣም መሰረታዊ ይዘቱን ሳይለቅ እንደ አስፈላጊነቱ በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ ወይም በፌዴራል ከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር አማካኝነት ሊሻሻል ይችላል፡፡

## 27. መመሪያው ስለሚጸናበት ሁኔታ

ይህ ሞዴል መመሪያ ከፀደቀበት ከ---ግንቦት 14---ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ጃንጥራር አባይ

የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር ሚኒስትር